በአማራ ብሔራዊክልላዊመንግሥት
ፍትሕ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር፡- የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/1026/18

ቀን 24/04/2018 ዓ/ም

ለመንገድ ትራንስፖርት ሎጅስቲክ ቢሮ
ባህርዳር፤

ጉዳዩ፡- መመሪያም ዝገባን ይመለከታል

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው በመላክ እንዲሁም አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አዋጁ በወጣ በ1 (አንድ) ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

በዚህ መሰረት የመንገድ፣ ትራንስፖርትና ሎጅስቲክ ቢሮ በቁጥር ት/ሎ/ባ/03-360/18 በቀን 24/03/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የከተማ ታክሲ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር የአደረጃጀትና አሰራር መመሪያ ቁጥር 13/2012 ዓ.ም ምዝገባ እንዲከናወን መላኩ ይታወሳል፡፡

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ ቁጥር 13/2012 ዓ.ም ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮና አስተካክሎ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 28/2018 ዓ.ም ሆኖ ስራ ላይ እንዲወል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ……ገጽ በዚህ ሽኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ሙሉጎጃም እንየዉ
በሕግ ምክር ፣ማርቀቅና
ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት
የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ//

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤ (ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

ፍትሕቢሮ

Tel.No 058 222 0794/793
☎ 058 220 37 57
✉ 995
Fax- 0582221530

# በአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ

# የከተማ ታክሲ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር አደረጃጀትና አሰራርመመሪያ ቁጥር 28/2018

ታህሳስ /2018

ባህር ዳር

# መመሪያ ቁጥር 28/2018 ዓ.ም

# በአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የከተማ ታክሲ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ

ትራንስፖርት ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት የጎላ ፋይዳ ካላቸዉ የአገልግሎት ዘርፎች አንዱ በመሆኑ ዘርፉን በተገቢዉ አግባብ ለመምራትያመች ዘንድ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሃብቶችን በማደራጀት አገልግሎቱ ዉጤታማና የተሳካ እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ስለሆነ፤

በክልላችን በፍጥነት እያደገ ያለዉን የከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት ግምት ዉስጥ ያስገባ አደረጃጀትና አሰራር መቅረጽ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ስራ ላይ ያለዉ የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ በርካታ ክፍተት ያለበት በመሆኑ አገልግሎቱን በአግባቡ ለመምራት የማያስችል ሁኔታ በመፈጠሩ፤

በትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ላይ የተሰማሩግለሰቦችና ድርጅቶች በግል ከመስራት ይልቅ በማህበር ተደራጅተዉ ቢሰሩ ለባለሃብቱ፣ ለህዝቡ እና ለመንግስትየሚሰጠዉ ጥቅም ከፍተኛ መሆኑን መንግስት በመገንዘቡበአዋጅ ቁጥር 468/97 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በማህበር ተደራጅተዉ እንዲሰሩበመፈቀዱ፤

የአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በተሻሻለው የአብክመ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ ማዳራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 264/2011 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 1(ሰ) ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የከተማ ታክሲ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ ቁጥር 28/2018 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ

1/ **"ቢሮ"** ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ነዉ፤

2/ **"መምሪያ"** ማለት በክልሉ የሚገኙ የዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያ ነዉ፤

3/ **"ጽህፈት ቤት"** ማለት በክልሉ የሚገኙ የወረዳ መንገድና ትራንስፖርት ጽ/ቤት እና የሶስቱ ሜትሮፖሊታንት ከተሞች ትራንስፖርት ጽ/ቤት ነዉ፤

4/ **"መካከለኛ ከተማ አስተዳደር ከተሞች"** ማለትበአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የከተሞች አደረጃጀት ፈርጅ መወሰኛና ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 65/2001 አንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 2 የተቀመጡ መመዘኛዎችን የሚያሟሉ ከተሞች ናቸው፤

5/ **"አነስተኛ ከተማ አስተዳደር ከተሞች"** ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የከተሞች አደረጃጀት ፈርጅ መወሰኛና ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 65/2001 አንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 3 የተቀመጡ መመዘኛዎችን የሚያሟሉ ከተሞች ናቸው፤

6/ **"መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች"** ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የከተሞች አደረጃጀት ፈርጅ መወሰኛና ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 65/2001 አንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 4 የተቀመጡ መመዘኛዎችን የሚያሟሉ ከተሞች ናቸው፤

7/ **"የትራንስፖርት ልማትቡድን"** ማለት ተጠሪነቱ ለዞን እና ለመካከለኛ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት ሆኖየከተማዉን የትራንስፖርት አገልግሎት ስራ እንዲመራ የተደራጀ ቡድን ነዉ፤

8/ **"የከተማ ታክሲ ተሽከርካሪ"** ማለት በከተማ ክልል ዉስጥ ሰዎችን ከቦታ ቦታ ለማመላለስ ኮድ አንድ ሰሌዳ የተሰጠዉ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነዉ፤

9/ **"የከተማ ታክሲ ተሽከርካሪ ባለንብረት"** ማለት በከተማ ክልል ዉስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ ከቢሮዉ ፈቃድ የተሰጠዉ ግለሰብ ወይም ድርጅት ነዉ፤

10/ **"ባጃጅ"** ማለት በከተማ ክልል ዉስጥ ሰዎችን ከቦታ ቦታ ለማመላለስ ኮድ አንድ ሰሌዳ የተሰጠዉ በሞተር ሃይል የሚንቀሳቀስና ባለ3 ጎማ ተሽከርካሪ ነዉ፤

11/ **"ሚኒባስ ታክሲ"** ማለትበከተማ ክልል ዉስጥ ሰዎችን ከቦታ ቦታ ለማመላለስ ኮድ አንድ ሰሌዳ የተሰጠዉ በሞተር ሃይል የሚንቀሳቀስና ባለ4 እና ከዚያ በላይ ጎማ ሆኖ ከ11 የማይበልጡ ሰዎችን የሚጭን ተሽከርካሪ ነዉ፤

12/ **"ሚዲባስ ታክሲ"** ማለት በከተማ ክልል ዉስጥ ሰዎችን ከቦታ ቦታ ለማመላለስ ኮድ አንድ ሰሌዳ የተሰጠዉ በሞተር ሃይል የሚንቀሳቀስና ባለ 4 እና ከዚያ በላይ ጎማ ሆኖ ከ12-24 ሰዎችን የሚጭን ተሽከርካሪ ነዉ፤

13/ **"የኤርፖርት ታክሲ"** ማለት በሞተር ሃይል የሚንቀሳቀስና ባለ 4 እና ከዚያ በላይ ጎማ ሆኖ ሰዎችን ከማረፊያቸዉ ወደ ኤርፖርት ከኤርፖርት ወደ ማረያፊያቸዉ የሚያጓጉዙ ኮድ አንድ ሰሌዳ የተሰጠዉና ቢጫ ቀለም የተቀባየታክሲ አገልግሎት የሚሰጥ ተሽከርካሪነው፤

14/ **"ማህበር"** ማለትበከተማ ታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 መሰረት የተቋቋመ የከተማ ታክሲ ባለንብረቶችማህበር ነው፤

15/ **"የስራ አመራር ቦርድ"** ማለት በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥና ማህበሩን የሚመራ አካል ነዉ፤

16/ **"የዉጭ ኦዲተር"** ማለት በስራ አመራር ቦርድ የሚመረጥ አግባብ ባለዉ መስሪያ ቤት ስለሙያዉ የተመሰከረለትና ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል የሂሳብ ምርመራ የሚያደረግ ግለሰብ/ ድርጅት ነዉ፤

17/ **"የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ"** ማለትየማህበሩ አባላት የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ላይ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ባያደርጉ በማህበሩ ውስጥ የተጠያቂነት አሠራር የሚኖርበትና የማህበሩ አባላት ተስማምተው ያፀደቁት ውስጠ ደንብ ነው፤

18/ **"ጊዚያዊ የማህበር አባል"** ማለትበአንድ ከተማ ዉስጥ የተደራጁየከተማ ትራንስፖርት ማህበራትየአባላት ቁጥር ሲሞላ እና ሌላ ማህበርማቋቋም እስከሚቻልድረስ አስቀድሞ በተመሰረተዉ ማህበር የስምሪት አገልግሎት ለማግኘት ሲባል በጊዚያዊነት የማህበር አባልመሆን ነዉ፤

19/ "ሰው"ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

20/ በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በክልላችን ባሉ የከተማ ታክሲ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበራት አባላት፣ የቦርድ አመራሮችና ቅጥር ሰራተኞች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር ስለማቋቋም እና ስለ ማህበር እድሳት

## 4. የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር አይነቶች እና ማህበር ለማቋቋም ማሟላት ያለባቸዉ መስፈርቶች

1/ ቢሮዉ አራት አይነት የታክሲ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር ፈቃድ ይሰጣል፡፡ እነርሱም፡-

ሀ) የባጃጅ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር፤

ለ) የሚኒባስ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር፤

ሐ) የሚዲባስ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር፤

መ) የኤር ፖርት ታክሲ ማህበር ናቸዉ፡፡

2/ ከላይ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸዉ ቢኖርም የሚኒባስ ታክሲ ወይም የሚዲባስ ታክሲ ባለንብረቶች አንድ ላይ ተደራጅቶ መስራት ፍላጎት ያላቸዉ መሆኑ ከተረጋገጠ የሚኒባስ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር ወይም የሚዲባስ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር በሚል ሊደራጁ ይችላሉ፡፡

3/ የታክሲ ተሽከርካሪ ባለንብረቶች በሚኖራቸዉ የተሽከርካሪ አይነት ከላይ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 ከተገለጹት አንዱን መርጠዉ ማህበር ማቋቋም ይችላሉ፡፡ ማህበር ለማቋቋም መሟላት ያለባቸዉ መስፈርቶች፡-

ሀ) ተሽከርካሪው የከተማ ታክሲ አገልግሎት ለመስጠትበክልሉ የተመዘገበ/ ኮድ1 ሰሌዳ የተሰጠዉ እና የወቅቱንአመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ያለፈ፤

ለ) ባጃጅ ሙሉ አካሉ ሰሚያዊ ቀለም፣ ሚኒባስና ሚዲባስ ታክሲከወገቡ በታችሰሚያዊ ከወገቡ በላይነጭ ቀለምየተቀባ መሆን አለበት፤

ሐ) የኤርፖርት ታክሲ ሙሉ አካሉ ቢጫ ቀለም የተቀባ እና የተሽከርካሪዉ አካል ላይ ወይም በሌላ አመቺ ቦታ ላይ በአማረኛ እና በእንግሊዘኛ ታክሲ የሚል ጽሁፍ የተጻፈበት፤

መ) የታክሲዉ ባለንብረት ጊዜዉ ያላለፈበት የንግድ ፈቃድ ያለዉ፤

ሠ) የታክሲዉ ባለንብረት የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ማቅረብ አለበት፤

ረ) የታክሲዉ ባለንብረት ጊዜዉ ያላለፈበትየሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ ማቅረብ፤

ሰ) የታክሲዉ ባለንብረት ጊዜዉ ያላለፈበት በክብደት ላይ የተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ክፍያ/የመንገድ ፈንድ/ የሚከፍል መሆኑን ማስረጃ ማቅረብ፣

ሸ) መስራች አባላት ከዚህ መመሪያ የማይቃረን የዉስጥመተዳደሪየ ደንብ በማዘጋጀት እና በመፈራረም በጽሁፍ በየደረጃዉ ላሉ መንገድና ትራንስፖርት መምሪያ/ ጽ/ቤቶች ጥያቄ ማቅረብ አለባቸዉ፤

ቀ) ለቢሮዉ የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም፡፡ይህዉም፡-

1) የባጃጅታክሲ ባለንብረቶች ማህበር

ሀ) የአባላት ብዛት እስከ50 ለሆነብር 100/ አንድ መቶ ብር/

ለ) የአባላት ብዛት ከ51-100 ለሆነብር 250/ ሁለት መቶ አምሳ ብር/

ሐ) የአባላት ብዛት ከ101-200 ለሆነብር 500/አምስት መቶ ብር/

መ) የአባላት ብዛት ከ201-300 ለሆነብር 750/ሰባት መቶ አምሳ ብር

ሠ) የአባላት ብዛት ከ301-400ለሆነብር 1000/ አንድ ሺህ ብር

2) ለሚኒባስ /ሚዲባስ እና የኤርፖርት ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር

ሀ) የአባላት ብዛት እስከ 50 ለሆነብር 200/ ሁለት መቶ ብር/

ለ) የአባላት ብዛት ከ51-100 ለሆነብር 500 /አምስት መቶ ብር/

ሐ) የአባላት ብዛት ከ101-200 ለሆነብር 800 / ስምንት መቶ ብር/

መ) የአባላት ብዛት ከ201-300 ለሆነብር 1100 /አንድ ሺህ አንድ መቶ ብር

ሠ) የአባላት ብዛት ከ 301-350 ለሆነብር 1500/አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር

## 5. የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበራት ሊይዙት የሚገባ አባላት ብዛት

1/ ቢሮዉ በአዋጅ ቁጥር 468/97 አንቀጽ 13 ተራ ቁጥር 2 በማህበር የሚታቀፉ አባልነት ቁጥር እንዲወስን በተሰጠዉ ስልጣን መሰረትአንድ የከተማ ታክሲ ማህበር የተሸከርካሪ ቁጥር ከዚህ በታች በተገለጸዉ አግባብ ይሆናል፡፡ይኸውም፡-

ሀ) የባጃጅ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር የተሸከርካሪቁጥር

1) በወረዳ ከተሞች ዝቅተኛዉ 20ከፍተኛዉ/ ጣሪያዉ/ 200
2) በመካከለኛ ከተሞች ዝቅተኛዉ40 ከፍተኛዉ/ ጣሪያዉ /300
3) በዞንከተሞችዝቅተኛዉ 50 ከፍተኛዉ/ ጣሪያዉ 350
4) በባህር ዳር ፣ጎንደር እና ደሴ ከተሞች ዝቅተኛዉ 100 ከፍተኛዉ/ ጣሪያዉ/400

ለ) የሚኒባስና የሚዲባስ ባለንብረቶች ማህበር የተሸከርካሪቁጥር

1) በወረዳ ከተሞች ዝቅተኛዉ 10 ከፍተኛዉ/ ጣሪያዉ / 150
2) በመካከለኛ ከተሞች ዝቅተኛዉ 20 ከፍተኛዉ/ ጣሪያዉ /200
3) በዞን ከተሞች ዝቅተኛዉ 30 ከፍተኛዉ/ ጣሪያዉ/250
4) በባህር ዳር ፣ጎንደር እና ደሴ ከተሞች ዝቅተኛዉ 50 ከፍተኛዉ/ ጣሪያዉ/350

ሐ/ የኤርፖርት ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር ዝቅተኛዉ 20ከፍተኛዉ /ጣሪያዉ/100

2/ ከላይ በአንቀጽ5 ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸዉ ቢኖርም ቢሮዉ በጥናት ላይ ተመስርቶ በአንድ ማህበር የሚታቀፉ የተሸከርካሪቁጥር ማሻሻያ ሊያደርግ ይችላል፤

3/ በአንድ ከተማ ዉስጥ አስቀድሞ በተመሰረተ ማህበር የተሸከርካሪ ቁጥር እስካልሞላ ድረስ ሌላ ማህበር ማቋቋም አይቻልም፡፡

## 6. የከተማ ታክሲ ትራንስፖርት ማህበራት ሊያማሏቸዉ የሚገቡ መስፈርቶች

1/ የሰው ሃይልበተመለከተ

ሀ) በሁሉም ከተሞች እና በሁሉም የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር የአባላት ብዛታቸዉ እስከ 50 የሆነ

1) የማህበር ጽ/ቤት ኃለፊ/ ስራ አስኪያጅ
2) ገንዘብ ያዥ

ለ) በሁሉም ከተሞች እና በሁሉም የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር የአባላት ብዛታቸዉ ከ51-200 የሆነ

1) የማህበር ጽ/ቤት ኃለፊ/ ስራ አስኪያጅ

2) የስምሪት እናየመረጃና የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ፈጠራ ባለሙያ

3) ገንዘብ ያዥ

ሐ) በሁሉም ከተሞች እና በሁሉም የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር የአባላት ብዛታቸዉ ከ200 በላይ የሆነ

1) የማህበር ጽ/ቤት ኃለፊ/ ስራ አስኪያጅ

2) የስምሪት ክትትልና ቁጥጥር ባለሙያ

3) የመረጃና የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ፈጠራ ባለሙያ

4) ገንዘብ ያዥ

መ) የሁሉም የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር ማህበሩ አገልግሎት በሚሰጥባቸዉ የስምሪት ጣቢያዎች የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጡንየሚቆጣጠር / ተራ የሚያስከብሩ/ ሰራተኛ መመደብ አለባቸዉ

ሠ) የሁሉም የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር ከላይ ከተገለጹትየስራ ክፍሎች ተጨማሪ ያስፈልገኛል ብሎ ካመነ ተጨማሪ የስራ ክፍል ማቋቋም ይችላል፡፡

ረ) የማህበሩ ተቀጣሪ ሰራተኞችከዚህ በታች የተገለጸዉን የትምህርት ዝግጅት ማሟላት አለባቸዉ፡፡ ይህዉም፡-

1) የማህበሩ ስራአስኪያጅ/ጽ/ቤት ኃላፊ/፡- የመጀመሪያ ድግሪ እና ከዚያ በላይ በማኔጅመንት፣በቢዝናስ አድሚኒስትሬሽን፣ በህዝብ አስተዳደር፣ በኢኮኖሚክስ፣ በህግ፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ ማኔጅመንት፣ ኢንጂነሪነግ፣ በመካኒካል ኢንጂነሪንግ፣ በአወቶሞቲቭ እናከላይ በተገለጹት የትምህርት ዝግጅቶች አቻ/ተመሳሳይ የትምህርት ዝግጅት ያለዉ፤

2) የማህበሩ የስምሪት ክፍል ኃላፊ፡-ዲፕሎማና እና ከዚያ በላይ በማኔጅመንት፣ በቢዝናስ አድሚኒስትሬሽን፣ በህዝብ አስተዳደር፣ በኢኮኖሚክስ፣ በህግ፣ በስታስቲክስ፣ በኮምፒዉተር ሳይንስ፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ ፣ማኔጅመንት፣ ኢንጂነሪነገ ፣ በመካኒካል ኢንጂነሪንግ ፣ በአወቶሞቲቭ እና ከላይ በተገለጹት የትምህርት ዝግጅቶች አቻ/ተመሳሳይ የትምህርት ዝግጅት ያለዉ፤

3) የማህበሩ የስምሪት እና የመረጃና የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ፈጠራ ባለሙያ፡-ዲፕሎማና ከዚያ በላይ በማኔጅመንት፣ በቢዝናስ አድሚኒስትሬሽን፣

በህዝብ አስተዳደር፣ በኢኮኖሚክስ፣ በህግ፣ በስታስቲክስ፣ በኮምፒዉተር ሳይንስ፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ ማኔጅመንት፣ ኢንጂነሪንግ፣ በመካኒካል ኢንጂነሪንግ፣ በአወቶሞቲቭ በስታስቲክስ፣ ማቲማቲክስ፣ ኢንፎርሜሽን ሳይንስ፣ በኮምኒኬሽን፣ በህግ፣ በአዉቶመካኒክ፣ በአዉቶሞቲቭእና በተገለጹት የትምህርት ዝግጅቶች አቻ/ተመሳሳይ የትምህርት ዝግጅት ያለዉ፤

4) ገንዘብ ያዥ/ የሂሳብ ባለሙያ /ኃላፊ -ዲፕሎማና እና ከዚያ በላይ በአካዉንቲንግ እና ተመሳሳይ፡፡

ሰ) የሰራተኛ ቅጥር ሲከናወንከአድሎ የነጻ አሰራር የተከተለ መሆን አለበት፤

ቀ) የሰራተኛ ቅጥር ሲከናወን በህግ ለሴቶች ተሰጣቸዉ ልዩ ጥቅምተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

2/ የቢሮ አደረጃጀት በተመለከተ

ሀ) የስራ አስኪያጅ ቢሮስፋቱ ቢያንስ 3ሜትር በ3 ሜትር የሆነና ደረጃዉን የጠበቀ ወንበርና ጠረንቤዛ እንዲሁም እንግዶች የሚያርፉበት ቢያንስ 4 ወንበር ያለዉ፤

ለ) ለእያንዳንዱ ሰራተኛ ስፋቱ ቢያንስ 2ሜትር በ3 ሜትር የሆነ ቢሮ ወይንም ሁሉንም ሰራተኛ ሊይዝ የሚችል ሰፊ ቢሮ ያለዉ ሆኖ በእያንዳንዱ ሰራተኛ ልክ ወንበርና ጠረንቤዛ እንዲሁም ባለጉዳዮች የሚያርፉበት ቢያንስ 2 ወንበር ያለዉ፤

ሐ) ቢያንስመደበኛ ስልክ እና ፋክስ ያለዉ፤

መ) ቢያንስ አንድ ኮምፒውተር እስከ ፕሪንተሩ ያለዉ፤

ሠ) ሰነዶች የሚቀመጡበትቢያንስአንድ የፋይል ካብኔት ወይም መደርደሪያ ሸልፍ፤

ረ) አንድ የከተማ ታክሲ ትራንስፖርት ማህበርፈቃድ በተሰጠዉ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለጹትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፤

ሰ) ከላይ በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 በፊደል ተራ ረ የተገለጸዉ ቢኖርም ማህበሩ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ አደረጃጀቱን ለማሟላት መቸገሩን በየደረጃዉ ላለዉ ለመንገድና ትራንስፖርት መዋቅር ካሳወቀ ተጨማሪ አንድ ወር ይሰጠዋል፤ በዚህ ጊዜ ዉስጥ አደረጃጀቱን ማሟላት ካልቻለ የተሰጠዉ ፈቃድ ይሰረዛል፡፡

## 7. ስለ ማህበር ፈቃድ እድሳት

1/ የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበርፈቃድ በየአመቱየሚታደስ ይሆናል፤

2/ አንድ የከተማ ታክሲ ማህበር ፈቃድ የተሰጠበትጊዜ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ዉስጥ የማህበሩን ፈቃድ ማሳደስ ይኖርበታል፤

3/ ከላይ በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተሰጠዉ ጊዜ በላይ ሶስት ወር አሳልፎ የመጣ ማህበርቅጣት ተቀጥቶ የማህበሩ ፈቃድ እድሳት የሚደረግ ሲሆን ከሶስት ወራት በላይ አሳልፎ የመጣ ማህበር ፈቃዱ አይታደስም፤ የማህበሩ ፈቃዱ ያልታደሰ ማህበር ፈቃዱ የተሰረዘ መሆኑን በጽሁፍ ይገለጽለታል፤

4/ ከላይ በአንቀጽ በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 3 በተገለጸዉ አግባብ ፈቃዱን የሚያሳድስ ማህበርበ እያንዳንዱ ላሳለፈበትቀን ብር 50 ሂሳብ እየተቀጣየማህበሩ ፈቃድ ይታደስለታል፤

5/ የማህበሩ ፈቃድ ሊታደስ የሚችለዉ፡-

ሀ) በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለጸዉ የሰዉ ሃይል፣ የቢሮ አደረጃጀት ተሟልቶ ሲገኝ፤

ለ) በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸዉ መሰረት የአባላት ቁጥር ተሟልቶ ሲገኝ፤

ሐ) የማህበሩ የፋይናንስ እንቅስቃሴ በህጋዊ የዉጪ ኦዲተር ተመርምሮና ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ሲጸድቅና በየደረጃዉ ላለዉ ለመንገድና ትራንስፖርት መዋቅር ተቀባይነት ሲያገኝ፤

መ) በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል ተራ ሀ-ረ የተጠቀሱት አሟልቶ ሲቀርብ፤

ሠ) ማህበሩ በፈጸመዉ ጥፋት ምክንያት ገንዘብ ተቀጥቶ ከሆነ የተቀጣዉን ገንዘብ መክፈል አለበት፡፡

6/ በእድሳት ወቅት መስፈርቱን ያላሟሉ የተሽከርካሪ ባለንብረቶች በሚኖሩበት ወቅት ከማህበሩ እንዲሰረዙ ተደርጎ መስፈርቱን ባሟሉ የተሽከርካሪ ባለንብረቶች ቁጥር ልክ ፈቃዱ ይታደሳል፤

7/ የማህበሩ ፈቃድ ሲታደስ ማህበሩ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ ቀ የተገለጸዉን የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፤

8/ በቅጣት የማህበር ፈቃድ ያሳደሰ ማህበር በቀጣይ አመት ፈቃዱ የሚታደሰዉ ፈቃዱ የተሰጠበትን ጊዜ ጠብቆ እንጂ ፈቃዱ የታደሰበተን ቀን ጠብቆ መሆን የለበትም፤

9/ ከመነሻ በታች የአባላት ቁጥር ይዘዉ የማህበር እድሳት እንዲደረግላቸዉ ጥያቄ የሚያቀርቡ ማህበራቶች ለአንድ በጀት አመት ብቻ ይታደስላቸዋል፡፡

# ክፍል ሶስት

## በጊዚያዊነት የማህበር አባል ስለመሆን፣ ከማህበር አባልነት መልቀቅ፣ መሰረዝ፣ ዝዉወር እና ማህበር ስለሚፈርስበት ሁኔታ

### 8. በጊዚያዊነት የማህበር አባል ስለመሆን

1/ በአንድ ከተማ ዉስጥ የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት የአባላት ቁጥር ከሞላ እና ሌላ ማህበር ለሟቋቋም የማይቻልበት ሁኔታ ሲፈጠር እና የሚደራጁበት ማህበር እስከሚገኝ ድረስ የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች በተሽከርካሪያቸዉ አይነት በመረጡት ማህበር በጊዚያዊነት የማህበር አባል በመሆን የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፤

2/ በጊዚያዊነት የማህበር አባል የሚሆኑ የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች እንደ ቋሚዉ የማህበር አባል የአገልግሎት ክፍያ በመክፍል የተሟላ አገልግሎት ማግኘት አለባቸዉ፡፡ግዴታቸዉንም መወጣት አለባቸዉ፤

3/ ከላይ በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸዉ ቢኖርም በተሽከርካሪያቸዉ አይነት የተደራጀ ማህበር ማግኘት ካልተቻለ የባጃጅ ባለንብረቶች በሚኒባስ/ በሚዲባስ ባለንብረቶች ማህበር እንዲሁም የሚኒባስ/ የሚዲባስ ባለንብረቶች በባጃጅ ባለንብረቶች ማህበር በጊዚያዊነት የማህበር አባል በመሆን መስራት ይቻላል፡፡ ነገር ግን የባጃጅ፣የሚኒባስና የሚዲባስ ባለንብረቶች በኤርፖርት ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር ፣የኤርፖርት ታክሲ ባለንብረቶች በባጃጅ፣ በሚኒባስና በሚዲባስ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር አባል መሆን አይችሉም፤

4/ በጊዚያዊነት የማህበር አባል የሆኑ የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች አዲስ ማህበር ለመመስረት የሚያስችል ቁጥር ላይ ሲደርሱ የራሳቸዉን ማህበር መመስረት አለባቸዉ ወይም ቢሮዉ ከየማህበሩ በጊዚያዊነት አባል የሆኑ የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች በማሰባሰብ ማህበር እንዲመሰርቱ ያደርጋል፤

5/ በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 4 በተገለጸዉ መሰረት ማህበር ለሚመሰርቱ የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች በጊዜያዊነት አባል አድርጎ ያቆያቸዉ ማህበር ቢያንስ ለምዝገባ የከፈሉት ገንዘብ ለሚደራጁበት ማህበር መመለስ ይኖርበታል፤

6/ በተለያዩ ምክንያቶች ከማህበር ጣሪያ በላይ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተደራጅተዉ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ እናበዚህ መመሪያ መሰረት የሚከፈሉ የከተማ ታክሲ ተሸከርካሪ ባለንብረቶች አዲስ ማህበር መመስረት አለባቸዉ፤

7/ ከላይ በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት አዲስ ማህበር የሚመሰርቱ የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች በጊዜያዊነት /በቋሚነት አባል አድርጎ ካቆያቸዉ ማህበር ሃብትና ንብረት/ የሰዉ ሃይል፣ ቋሚና አላቂ ንብረት/ የመካፈል ፍላጎት ካላቸዉ ከነባሩ ማህበር የስራ አመራር ቦርድ፣ በአዲስ መልክ ከሚደራጀዉ ማህበር አባላት እና ከአደራጁ መ/ቤት የተዉጣጣ ኮሚቴ በማቋቋም ኮሚቴዉ በፍትሃዊ ሁኔታ አስፈላጊዉ የሃብት ክፍፍል ያደርጋል፤

8/ ከላይ በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 7 በተገለጸዉ መሰረት የሰዉ ሃይል ክፍፍል በሚደረግበት ወቅት ነባሩ ማህበር በዉስጡ የያዛቸዉን ሁሉንም ሰራተኞች ይዞ የመቀጠል ፍላጎት ካለዉ ይዞ መቀጠል ይችላል፤ ነገር ግን ማህበሩ በዚህ መመሪያ ከሚጠይቀዉ የሰዉ ሃይል በላይ ያለዉ ከሆነ በአዲስ መልክ የሚመሰረተዉ ማህበር ትርፍ የሆኑትን ሰራተኞች መያዝ ይኖርበታል፤ በመሆኑም በነባሩ ማኅበር ተቀጥረው ይሠሩ የነበሩ ሠራተኞች ተፈላጊ መስፈርቱን እስካሟሉ ድረስ በማህበራቱ መካከል በሚደረግ ስምምነት እንዲደለደሉ ይደረጋል እንጂ ሠራተኛው ከሥራው የሚፈናቀልበት ዕድል መኖር የለበትም፡፡

## 9. ከማህበር አባልነት ለመልቀቅ የሚያስችሉ ሁኔታዎች

1/ የማህበር አባል ከማህበሩ በራሱ ፈቃድ ለመልቀቅ የጽሁፍ ማመልከቻ ሲያቀርብና ከማህበሩ በሰነድ የወሰደውን ንብረት በሰነድ ወይም በአይነት ወይም በገንዘብ ካስረከበ ማህበሩን ሊለቅ ይችላል፤

2/ መልቀቂያ እንዲሰጠዉ በጽሁፍ ያቀረበ አባል ከላይ በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸዉ ግዴታ እስከተወጣ ድረስ እጅግ ቢዘገይ እስከ አምስት ቀናት ዉስጥ መልቀቂያ ሊሰጠዉ ይገባል፤

3/ ከላይ በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸዉ መሰረት መልቀቂያ የተሰጠዉ የተሽከርካሪ ባለንብረት የጸደቀለት የስራ መርሃ ግብር እስከሚጠናቀቅ ድረስ አገልግሎት መስጠት አለበት፤

4/ በመልቂቂያ አሰጣጥ ሂደት በአባሉና በማህበሩ መካከል መግባባት ካልተቻለ በሚቀርበዉ ጥያቄ መሰረት ለማህበሩ ፈቃድ የሰጠዉ ቢሮ/ መምሪያ/ ጽ/ቤት ጣልቃ በመግባት ችግሩ እንዲፈታ ያደርጋል፤

5/ መልቀቂያ የተሰጠዉ የተሽከርካሪ ባልንብረት በክልሉ ዉስጥ በተቋቋመ ሌላ ማህበር ለመደራጀት ፍላጎት ካለዉ ቀድሞ ከነበረበት ማህበር የተሰጠዉን መልቀቂያ በማቅረብ መደራጀት ይችላል፤

6/ መልቀቂያ የተሰጠዉ የተሽከርካሪ ባለንብረት ወደ ነበረበት ማህበር ለመመለስ ከፈለገ እና ቅድመ ሁኔታዎችን ከሟላ ጥያቄዉን ለስራ አስኪያጁ በማቅረብ ተቀባይነት ካገኘ መመለስ ይችላል፤

7/ ማህበሩ በተለያየ ምክንያቶች የለቀቁ የከተማ ታክሲ የተሽከርካሪ ባለንብረቶች መረጃ ፈቃድ ለሰጠዉ ጽ/ቤት ወይም መምሪያ በአንድ ሳምንት ዉስጥ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 10. ከማህበር አባልነት ለመሰረዝ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች

1/ አባሉ በማህበሩ የዉስጥ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ከማህበሩ አባልነት ሊያሰርዘዉ የሚያስችሉ ተጨባጭ ጥፋቶች አጥፍቶ ሲገኝ እና ስረዛዉ በሁሉም የስራ አመራር ቦርድ ሲጸድቅ፤

2/ አባሉ ከማህበሩ እዉቅና ዉጪ ያለበቂ ምክንያት ለተከታታይ 10 ቀናት የስምሪት አገልግሎት መስጠት ካቋረጠ፤

3/ በዚህ መመሪያ ዉስጥ ከማህበር አባልነት ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋቶች ፈጽሞ ሲገኝ፤

4/ አባሉ በራሱ ጊዜ ማህበሩን መልቀቅ ከፈለገ፤

5/ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 3 በፊደል ተራ ሀ፣ መ፣ ሠ እና ረ የተገለጹት ሳይሟላ ሲቀር፤

6/ አባሉ በሞት ሲለይ፤

7/ ማህበሩ በተለያየ ምክንያቶች የሰረዛቸዉን የከተማ ታክሲ የተሽከርካሪ ባለንብረቶች መረጃ ፈቃድ ለሰጠዉ ጽ/ቤት ወይም መመሪያ በአንድ ሳምንት ዉስጥ ማሳወቅ አለበት፤

8/ በአንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 ከማህበር አባል የተሰረዘ አባል እንዲሰረዝ ያበቃዉ ከአቅም በላይ ችግር መሆኑን ማስረጃ ካቀረበና ማስረጃዉ በአደራጁ አካል ተቀባይነት ካገኘ ሳይቀጣ በአዲስ መልክ ተመዝግቦ ይደራጃል፤ ያቀረበዉ ማስረጃ በአደራጁ አካል ተቀባይነት ካለገኘከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ለእያንዳንዱ 15 ቀናት ብር 300 ተቀጥቶ ወደ አባልነት እንዲመለስ ይደረጋል፤

9/ በአንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 3 ከማህበር አባል የተሰረዘ አባል እንዲሰረዝ ያበቃዉ ከአቅም በላይ ችግር መሆኑን ማስረጃ ካቀረበና ማስረጃዉበአደራጁ አካል ተቀባይነት ካገኘ ሳይቀጣ በአዲስ መልክ ተመዝግቦ ይደራጃል፤ ያቀረበዉ ማስረጃ በአደራጁ አካል ተቀባይነት ካለገኘ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ለእያንዳንዱ 15 ቀናት ብር 100 ተቀጥቶ ወደ አባልነት እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

## 11. ከአንድ ማህበር ወደ ሌላ ማህበር ዝዉዉር ስለማድረግ

1/ ለዝውውር የሚያበቁ ቅድመ ሁኔታዎች

ሀ) በሽያጭ ምክንያት ሊብሬው በገዢው ስም ሲዛወር እና ገዥው ወደ ሌላ ማህበር ለመዛወር ጥያቄ ሲያቀርብ፤

ለ) እንደ ማህበር አባልነት እኩል አገልግሎት ባለማግኘቱና ሌሎች ተያያዥ ችግሮችና አለመግባባቶች በባለንብረት እና በማህበሩ መካከል ሲከሰት እና ይኸው በሕጋዊ ማስረጃ ሲረጋገጥ፤

ሐ) የማህበሩ ተሽከርካሪ ቁጥር ከተደራጀበት መስፈርት በታች ሲሆን የዝውውር ጥያቄ ከቀረበ የአባላት ዝውውር በቢሮዉ ሲፈቀድ፡፡

2/ ዝውውር የሚያስከለክሉ ጉዳዮች

ሀ) በማህበሩ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ እና በማህበራት አደረጃጀት መመሪያ መሠረት ጥፋት አጥፊቶ እርምጃ የተወሰደበት ባለንብረት ለአንድ አመት ከዝውውር ይታገዳል፤

ለ) ማንኛውም ባለንብረት የማህበር ዕዳ ካለበት ሙሉ በሙሉ ከፍሎ እስከሚጨርስ ድረስ የዝውውር ጥያቄ ሊያቀርብ አይችልም፤

ሐ) ማንኛውም ባለንብረት የማህበር እዳ ካለበት ወደ ሌላ ማህበር ለመዛወር ከፈለገ የሁለቱ ማህበራት ስምምነት ለአደራጁ አካል ማቅረብ ካልቻለ የዝውውር ጥያቄ ሊያቀርብ አይችልም፤

መ) ማንኛውም አባል በአዲስ መልክ ወደ ተዛወረበት ወይም አዲስ በተቋቋመበት ማህበር ቢያንስ ከአንድ ዓመት የቆይታ ጊዜ በኋላ ወደ ሌላ ማህበር ዝውውር መጠየቅ አይችልም፡፡

12. **ስለማህበር መፍረስ**

1/ የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሊፈርስ ይችላል፡-

ሀ) የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤው 3/4ኛ የአባልነት ድምጽ ብልጫ ማህበሩ እንዲፈርስ ሲወስኑ እና ዉሳኔዉ በየደረጃዉ ላለዉ ለመንገድና ትራንስፖርት መዋቅር ቀርቦ ሲፀድቅ፤

ለ) ማህበሩ እንዲፈርስ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሲሰጠዉ፤

ሐ) የማህበር አባላት ቁጥር ከመነሻ አባለት ቁጥር በታች ሆኖ ሲገኝ፤

መ) የማህበሩ ፈቃድ በወቅቱ ካልታደሰ እና በዚህ መመሪያ ማህበሩን ሊያሰረዝ የሚያስችል ሊሎች ጥፋቶች ፈጽሞ ሲገኝ፡፡

2/ ከላይ በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል ተራ ሀ እና ለ በተጠቀሱት ምክንያቶች ማህበሩ ከፈረሰ የማህበሩ ገንዘብና ንብረት በፍትህ ብሔር ህግ ቁጥር 467 በተደነገገው መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል

3/ ከላይ በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል ተራ ሐ እና መ በተጠቀሱት ምክንያቶች የፈረሰ ማህበር የማህበሩ አባላቶች ያላቸዉን ሃብትና ንብረት ይዘዉ ወደ ሌላ ማህበር እንዲቀላቀሉ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## የከተማታክሲ ትራንስፖርት ማህበራት ገቢ እና የማህበር ሂሳብ ስለማስመርመር

13. **የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት ገቢ**

የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት የፋይናንስ ምንጮች፤-

1/ የአገልግሎት ክፍያ/ኮሚሽን፤

2/ ከአባላት ቅጣት፤

3/ አባላት ከሚያደርጉት ልዩ ልዩ መዋጮ፤

4/ ከአባላት የመመዝገቢያ ክፍያ ሲሆን የአባለት መመዝገቢያ ክፍያ የገንዘብ መጠን እንደማህበሩ ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ ከብር1000 መብለጥ የለበትም::

## 14. የማህበር ሂሳብ ስለማስመርመር

1/ የማህበሩ ፈቃድ ማደሻ ጊዜ እንደተጠናቀቀ የማህበሩ ሂሳብ በውጭ ኦዲተር ተመርምሮ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ መጽደቅ ይኖርበታል፤

2/ የኦዲት ሪፖርቱ በጠቅላላ ጉባኤ በፀደቀ ከ15-30 ቀናት ዉስጥ ለአደራጁ አካል መቅረብ አለበት፡፡

# ክፍል አምስት

# የከተማ ታክሲ ትራንስፖርት ማህበራት ተግባርና ኃላፊነት፤ የአባላት መብትና ግዴታ እና የማህበራት አደረጃጀትና ስልጣንና ተግባር

## 15. የከተማ ታክሲ ትራንስፖርት ማህበራት ተግባርና ኃላፊነት

የከተማ ታክሲ ትራንስፖርት ማህበራት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፡-

1/ በማህበር አባላትነት ለመመዝገብ የሚፈልጉ እና መመዘኛውን የሚያሟሉ ኦፕሬተሮች የዘር የሃይማኖት የጾታ እና የፖለቲካ ልዩነት ሳይደረግባቸው በአባልነት መመዝገብ፤

2/ የማህበሩ ቅጥር ሠራተኞች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነትና ተግባር እንዲወጡ በማድረግ በሚፈፅሟቸው የስነ ምግባር ችግሮች በመከታተል የእርምት እርምጃ መዉሰድ፤

3/ የማህበሩ እዉቅና በተሰጠዉ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ በማህበሩ ስም የባንክ አካውንት ከፍቶ በተከፈተዉ አካዉንት ገንዘብ ገቢ ማድረግ፤

4/ በታክሲ ማሽከርከር ተግባር ላይ የተሰማሩ አሽከርካሪዎች የሚያደርሡትን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ የግንዛቤ ማዳበሪያና የተሃድሶ ስልጠና የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት፤

5/ የማህበሩ አባል ጥሩ ስነ ምግባር ያላዉ አሽከርካሪ እና ረዳት/ ገንዘብ ያዥ እንዲቀጠሩ ማድረግ፤

6/ ስለመንገድ ትራንስፖርት የወጡ ህጎችን ደንቦችና መመሪያዎችን አባላት እንዲያውቁትና አክብረው እንዲያስተገብሩ ማድረግ፤

7/ የማህበሩን አባላት የስራ አቅም በማጐልበትና የሙያ ብቃት በማሳደግ የአገልግሎት አሠጣጡ ላይ መሻሻል እንዲታይአስፈላጊዉን ጥረት ማድረግ፤

8/ የማህበሩ አባላት የሚሠጡት አገልግሎት የተሟላ እንዲሆን የተሽከርካሪዎች ቴክኒካል ብቃት ጠብቀው የሚቆዩበት እንዲሁም ማህበሩ ወደ ማስ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚያድጉበትን ሁኔታ ማሟላት፤

9/ ለማህበሩ አባላት ተሽከካሪዎች መነሻና መድረሻ ታፔላ ማዘጋጀትና ስራ ላይ እንዲዉል ማድረግ፤

10/ የተሽከርካሪ ባለንብረቶች የአባልነት ጥያቄ ሲያቀርቡ ከነበሩበት ማህበር መልቀቂያ የተሠጣቸውና ችግር የሌለባቸው መሆኑን በማረጋገጥ በአባልነት መመዝገብ ይኖርበታል፣

11/ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና ሰነዶችን በሚገባ መያዝና በቢሮዉ ሲጠየቅም ማቅረብ፤

12/ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ባጸደቀው መሰረት ከአባላት ኮሚሽን መሰብሰብ፤

13/ የማህበሩ አባላት ሕግና ደንብን ጠብቀው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፤

14/ አባላቱን በመወከል የስራ ውሎችን ማካሄድ::

## 16. የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት አባላቶች የሚከተሉት መብቶች ይኖራቸዋል

1/ በማህበሩ ዉስጥ የመምረጥም ሆነ የመመረጥ፤

2/ ማህበሩ ለአባላቱ በሚሰጠዉ ማንኛዉም አገልግሎት እኩል የመጠቀም፤

3/ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ማህበሩ የሚመራባቸዉን መመሪያዎችና አደራጅ አካል በየጊዜዉ የሚያወጣቸዉን መመሪያዎች የማግኘት፤

4/ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች ላይ መገኘት፣ ለማህበሩ የተሻለ የስራ እንቅስቃሴ መፈጠር የሚረዱ አስተያየቶችና የዉሳኔ ድምጽ የመስጠት መብት ይኖረዋል፤ በዚህም መሰረት አንድ አባል አንድ ድምጽ ይኖረዋል፤

5/ በማህበሩ መደበኛና አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች ላይ ተገኝቶ ተሳትፎ ማድረግ፤

6/ በመንግስትም ሆነ በማህበሩ የስራ አመራር ቦርድ መስተካከል አለባቸዉ የሚላቸዉን ችግሮች እንዲስተካከሉ የመጠየቅ፤ ካልተፈጸመም ለአደራጁ አካል ማሳወቅ፡፡

## 17. የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት አባላቶች የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖራቸዋል

1/ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የስልጣን ዉክልና በተሰጠዉ የስራ አመራር ቦርድ የሚተላለፉ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን መፈጸም፤

2/ በመንግስት የሚወጡ ህጎች ደንብና መመሪያዎችን አክብሮ በስራ ላይ ማዋል፤

3/ በጠቅላላ ጉባኤ የሚወሰኑ ልዩ ልዩ ክፍያዎች መክፈል፡፡

## 18. የከተማ ታክሲ ትራንስፖርት ማህበራትአደረጃጀትና ስልጣንና ተግባር

1/ አደረጃጀት

ሀ) አንድ የከተማ ታክሲ የትራንስፖርት ማህበር ከአምስት እስከ ሰባት አባላት ያሉትየሥራ አመራሮችን ሊመርጥ ይችላል፤

ለ) የስራ አመራር ቦርድ ሆነዉ የሚመረጡ ሰዎች የትምህርት ዝግጅታቸዉ ዲፕሎማና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፤

ሐ) ከላይ በአንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል ተራ ለ የተገለጸዉ ቢኖርም በማህበሩ ዉስጥ ዲፕሎማና ከዚያ በላይ የትምህርት ዝግጅት ያለዉ አባል ካልተገኘ በቀድሞ 12 በአሁኑ 10 ክፍል ያጠናቀቀ መሆን አለበት፤

መ) የስራ አመራር ቦርድ ምርጫ በሚደረግበት ወቅት ቅድሚያ ከፍተኛ የትምህርት ዝግጅት ለሚኖራቸዉአባላቶች እድል መስጠት አለበት፤

ሠ) የስራ አመራር ቦርድ የስራ ዘመን ሁለት አመት ይሆናል፤

ረ) አንድ አባል በስራ አመራር ቦርድ በተከታታይ ከሁለት የስራ ዘመን በላይ መመረጥ አይችልም፤ ሆኖም ግን ከአራት አመት ቆይታ በኋላ እንደገና ሊመረጥ ይችላል፤

ሰ) በማህበሩ ዉስጥ መስፈርቱን የሚያሟሉሴት አባለት ካሉ የስራ አመራር ቦርድ ምርጫ በሚደረግበት ወቅት ቢያንስ አንዲት ሴት መመረጥ አለባት፤

ሸ) በማሕበሩ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ለሥራ አመራር ቦርድ አባልነት መመረጥእና መምረጥ የሚችሉት የተሸከርካሪ ባለንብረት የሆኑ ብቻ ናቸዉ፤

ቀ) ሥራ አመራር ቦርድ አባል በማህበሩ ውስጥ በሥራ አስኪያጅነትም ሆነ በሌሎች የሥራ ክፍሎች ውስጥ ተመድቦ መሥራት አይችልም፤

በ) የስራ አመራር ቦርድ የራሱ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ ፀሐፊና ኦዲትና ኢንስፔክሽንይኖሩታል፤

ተ) የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ያለድምፅ የሥራ አመራር ቦርዱ ፀሐፊ ይሆናል፤

ቸ) የሥራ አመራር ቦርዱ እንደአስፈላጊነቱ በንኡሳን ኮሚቴዎች ሊደራጅ ይችላል፡፡

2/ ስልጣንና ተግባራት

ሀ) የጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

1) ለማህበሩ የስራ እንቅስቃሴ ተጠንቶ የቀረበለትን የስራ ዕቅድና ማስፈጸሚያ በጀት መርምሮ ያጸድቃል፤

2) የማህበሩን የስራ አመራር ቦርድ አባላትን ይመርጣል፣ ይሽራል እንዲሁም ስልጣንና ተግባራቸውን ይወስናል፤

3) የኦዲትና ኢንስፔክሽን አባላትን ከማሕበሩ አባላት መካከል ይመረጣል፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ይወስናል፤

4) የማህበሩን የስራ አመራር ቦርድ አባላትና በጠቅላላ ጉባኤ ለሚመረጡ የሥራ አካላት ለሚሰጡት አገልግሎት እንደአስፈላጊነቱ የሥራ አበል ይወስናል፤

5) የስራ አመራር ቦርዱን የስራ ሪፖርት ያደምጣል፣ በጀት ያሻሽላል፣ ሪፖርት መርምሮ ያጸድቃል፤

6) በሥራ አመራር ቦርዱ ተወዳድረውበሚቀርቡለት መሰረት ለሚቀጥሉት ሁለት አመት የሚሰራ የውጭ ኦዲተር ይመርጣል፤

7) ከስራ አመራር ቦርድ በሚቀርብለት መሰረትም የማህበሩን ጽ/ቤት ኃላፊ/ ስራ አስኪያጅ ቅጥር መርምሮ ያጸድቃል፤

8) የማህበሩን ንብረት አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም የፋይናንስ ወጭና ገቢ ሂሳብን በተመለከተ ወቅቱን ጠብቆ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ውጤቱ በሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤

9) ማሕበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ መሰረት በማድረግ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የማሕበሩን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ያጸድቃል፣ ያሻሽላል፤

10) በአባላት የሚከፈለውን የአገልግሎት መዋጮና የመመዝገቢያ ክፍያ መጠን ይወስናልያሻሽላል፤

11) ለማህበሩ ዕድገት በስራ አመራር ቦርድ ተጠንቶ የሚቀርቡለትን የአሰራር ማሻሻያ ጥናቶችን መርምሮ ያፀድቃል፣ ተግባራዊ እንዲሆንም መመሪያ ይሰጣል፣

12) በማሕበሩ መፍረስ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

13) የሥራ አመራር ቦርድ አባላት የሚፈፅሙትን የስራ ግድፈትና ሕገወጥ ተግባራት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

14) የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ የሚመሩ አካላትን በየስብሰባው ይመርጣል፣ የሥራ መመሪያም ይሰጣል።

ለ) የስራ አመራር ቦርድ ስልጣንና ተግባር

1) ለከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት ባለንብረቶች የተሰጡትን ተግባርና ሃላፊነቶች በባለቤትነት ይዞ ይመራል ያስተባብራል፤

2) የሥራ አመራር ቦርዱ የማህበሩን ሥራ አስኪያጅ በስነ-ምግባሩ ምስጉን የሆነ እና የማህበር አባል ያልሆነ አወዳድሮ ይቀጥራል፣ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦም ያፀድቃል፣ ተገቢው የሥራ መዘርዝር ተዘጋጅቶ እንዲሰጠው ያደርጋል፤

3) የሥራ አመራር ቦርዱ በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን መመሪያዎችና የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ስራ ላይ ያውላል፤

4) የማህበሩን የሥራ ዕቅድና ማስፈፀሚያ በጀት ያዘጋጃል፣ በጠቅላላ ጉባኤ ሲፀድቅም ስራ ላይ ያውላል፤

5) የማህበሩን ሥራ ለማከናወን የሚያስችል ጽህፈት ቤት ያደራጃል፤

6) የማህበሩን የፋይናንስ እንቅስቃሴ በሕግና ስርዓት እንዲመራ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣ አመራርም ይሰጣል፤

7) በጠቅላላ ጉባኤው ምርጫ መሰረት የሥራ አመራር ቦርዱ ከቦርዱ በሚወክለው ቦርዱ አባልና የጽ/ቤት ሙያተኛ አማካይነት በማሕበሩ ስም የባንክ ሂሳብ በመክፈት ያንቀሳቅሳል፤

8) የስራ አመራሩ በሚወስነው የገንዘብ መጠን መሰረት የአመራሩ ቦርድ ሰብሳቢ፣ ስራአስኪያጅ እና የፋይናንስ ክፍል ጣምራ ፊርማ የማህበሩን ገንዘብ ማንቀሳቀስ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ሂሳቡን በወቅቱ ማወራረድ አለበት፤

9) የማህበሩ የስራ እንቅስቃሴ የሚገልጽ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፤ በሪፖርት ዝግጅት ሂደት ሥራ አስኪያጅ የሚጠበቅበትን የሥራ ድርሻ መውጣት እንዲችል ተገቢው አመራር ለሥራ አስኪያጅ መስጠት ይኖርበታል፤

10) የማህበሩን ዓመታዊ ንብረትና ሂሳብ መስፈርት በጠበቀ አሰራር ሕጋዊ ኦዲተር አወዳድሮ በጠቅላላ ጉባኤው አፀድቆእንዲመረመር ያደርጋል፤

11) የተጓደሉ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ሲኖሩም የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ በመጥራት በምትክ ምርጫ እንዲያሟላ ያደርጋል፤

12) በዘርፉ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በቢሮው የሚተላለፉ መመሪያዎችን ተቀብሎ ይፈጽማል፣ በአባላቱም እንዲፈፀሙ ያደርጋል ተግባራዊነቱንም ይቆጣጠራል፤

13) የማህበሩን አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ ይመራል፣ በየደረጃውም ለሚሰጠው አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑትን የሥራ አካላትን በማዋቀርና በሙያተኞችም በማጠናከር እንዲሰሩ ያስደርጋል፣ የሥራ አፈፃፀማቸውንም ይቆጣጠራል፤

14) የማህበሩን ኦፕሬሽናል ስራዎች የሚገልፅ መረጃ ለቢሮው መተላለፉን ያረጋግጣል፣ በአስፈላጊ ወቅት የሚጠየቁ መረጃዎች በወቅቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፤

15) ማህበሩ ለትርፍ የተቋቋመ ባለመሆኑ የማህበራት ንብረትና ገንዘብ ለአባላቱ የጋራ ጥቅም በሚውሉ የተጠኑ ሥራዎች ላይ ከማዋል ባለፈ ከሕግ አግባብ ውጭ ክፍፍል እንዳይፈፀም ያደርጋል፤

16) ከተመረጠበት የሥራ አመራር ቦርድ አባልነት ውጭ በማህበሩ የሙያዊ አገልግሎት ላይ ወይም በማሕበሩ ሥራ አስኪያጅነት በኃላፊነት ተመድቦ መሥራት አይችልም፡፡

ሐ) የሥራ አመራር ቦርድ ሊቀመንበር ተግባርና ኃላፊነት፡-

1) የቦርዱን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፤
2) በየደረጃው ያሉትን የማሕበሩን የሥራ አካላት እንቅስቃሴ በበላይነት የሚመራውን የማህበሩን ሥራ አስኪያጅ ይደግፋል፣ ያስተባብራል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይቆጣጠራል፤
3) በጠቅላላ ጉባኤው የተሰጡ አመራርና የተወሰኑ ውሳኔዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤
4) ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርቶችን የሥራ አመራር ቦርዱን በመወከል ለማሕበሩ ጠቅላላ ጉባኤያቀርባል፤
5) ማህበሩን በመወከል አስፈላጊ ስብሰባዎችን፣ ስልጠናዎችን ይካፈላል፣ ወይም ከቦርዱ አባላት የተወከሉ ክፍሎች እንዲካፈሉ ያደርጋል፤
6) አስፈላጊ ሲሆን ከመደበኛ ስብሰባ ውጭ የሥራ አመራር ቦርዱን አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል፡፡

መ) የስራ አመራር ቦርድ ምክትል ሊቀመንበር ሥልጣንና ተግባር

1) ሊቀመንበሩን በቅርብ በመሆን ያግዛል፤
2) ሊቀመንበሩ ሳይኖር ቦታውን ተክቶ ይሰራል፤
3) በሊቀመንበሩ ተለይተዉ የሚሰጡ ተግባራቶች ያከናዉናል፡፡

ሠ) የስራ አመራር ቦርድ ፀሃፊ ተግባርና ኃላፊነት

1) የቦርዱን ስብሰባ አጀንዳዎች ከሰብሳቢው ጋር በመነጋገር ያዘጋጃል፣ ይህንኑ አጀንዳም ለሥራ አመራር ቦርድ አባላት ከስብሰባው 3 ቀናት በፊት እንዲደርስ ያደርጋል፤
2) የቦርዱን ስብሰባ አጀንዳዎች ከሰብሳቢው ጋር በመነጋገር ያዘጋጃል፣ ይህንኑ አጀንዳም ለሥራ አመራር ቦርድ አባላት ከስብሰባው 3 ቀናት በፊት እንዲደርስ ያደርጋል፤
3) የስራ አመራር ቦርዱ የሚያደርገውን ስብሰባ ቃለጉባኤ መዝግቦ ይይዛል፣ የስብሰባውን ሰነድም በቦርዱ አባላት ፊርማ እንዲፀድቅ እና በሰነድነትም እንዲያዝ ያደርጋል፤
4) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአደራጁ አካል መረጃና ማብራሪያ ሲጠየቅ መልስ ይሰጣል፡፡

ረ) የኦዲትናኢን ስፔክሽን ሥልጣንና ተግባር

ጠቅላላ ጉባኤው ከአባላቱ መካከል ችሎታና ብቃት ያላቸውን 3 አባላት መርጦ ኦዲትና ኢንስፔክሽን አካል ይሰይማል፣ ይህ አካል ተጠሪነቱም ለጠቅላላ ጉባኤውሆኖ የሚከተሉትን ተግባርና ሃላፊነቶች ያከናውናል፡-

1) የማህበሩን የንብረትና ፋይናንስ አሠራር፣ አደረጃጀትና አጠቃቀም እንዲሁም የሥራ መዛግብትን በሕግ መሠራቱን ይከታተላል፤
2) የማኀበሩን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴዎች በዕቅድ መሠረት መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፤
3) በማሕበሩ አመራር አካላት ውስጥ ወይም በአመራር አካላቱና በአባላቱ መካከል የሥራ ችግሮች ሲፈጠሩ ቅሬታውን አጣርቶ ከመፍትሄ ሃሳብ ጋር ለሥራ አመራር ቦርዱ ያስተላልፋል፤
4) ዓመታዊ የሥራ ክንውኖችን በመመርመርና ውጤታቸውንም በመለየት የሥራ ውጤቱን በዝርዝር አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት ያቀርባል፤

5) በአሠራር ላይ የተለዩ ችግሮችን አጥንቶ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤

6) ጠቅላላ ጉባኤው በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት አመታዊ ስብሰባ ሳይካሄድ ከቀረ፣ ወይም በአባላቱ 1/3ተኛ የቀረበን የስብሰባ ጥሪ ጥያቄ መሠረት በማድረግ ስብሰባ ካልተደረገና በማህበሩም አመራር ከፍተኛ የአሠራር ችግር መኖሩን ካረጋገጠ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራ ያደርጋል፤

7) የሥራ ክንውን ሪፖርቱንም ለአደራጁ አካል ስብሰባውእንዳበቃ በፅ/ቤቱ በኩል እንዲደርስ ያደርጋል።

ለ) የማህበሩ ተቀጣሪ ሰራተኞች ሥልጣንና ተግባር

1) የማህበሩ ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ስራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባርና ኃለፊነቶች የማህበሩ ጽ/ቤት ሃላፊ ወይም ሥራ አስኪያጅ ቀጥታ ተጠሪነቱ ለማሕበሩ የሥራ አመራር ቦርድ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የስራ አመራር ቦርድ ስብሰባዎች ላይ በአስረጅነት ያለ ድምጽ ይሳተፋል በፀኃፊነትም ያገለግላል፤

ለ) ከማህበሩ የሥራ አመራር ቦርድ በሚሰጠው የስራ መመሪያ መሰረት የማህበሩን ጽ/ቤት በማዋቀርና በሙያተኛ በማጠናከር ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

ሐ) ማህበሩ ለሚሰጠው አገልግሎት ከሚመለከታቸው ጋር የስራ ውሎችን ይዋዋላል፣ የመፃፃፍ ስራዎችን ያከናውናል፣ ማህበሩን ወክሎም ይከሳል ይከሰሳል፤

መ) ለማህበሩ የሥራ እንቅስቃሴ አስፈላጊ የሆኑትንና በስሩ ያሉትን የሥራ ክፍሎች ያዋቅራል፣ የሥራ ዕቅድና ማስፈፀሚያ በጀት አጥንቶ ያቀርባል፣ ለቦርዱም አቅርቦ ያፀድቃል፤

ሠ) በሚፈቀድለት የሥራ ማስፈፀሚያ በጀት መሠረት ለሥራው የሚያስፈልጉ የስራ አካላትና አወዳድሮ በመቅጠር ለሥራ አመራር ቦርዱ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡ ለሥራ ክፍሎቹም ሠራተኞች የሥራ መመሪያና ዝርዝር የሥራ ድርሻ በማዘጋጀት ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

ረ) ለማሕበሩ ሥራ የሚያስፈልጉ ሠራተኞችን ቅጥርና ስንብት ያከናውናል፤

ሰ) ከሥራ አመራር ቦርዱ በሚሰጠው የስልጣን ውክልና መሰረት ከአመራር ቦርዱ ከሚወከሉ አባላት ጋር በሆን የማሕበሩን ቼክ ይፈርማል፣ የወጪ ክፍያዎችን ይፈቅዳል፣ ያፀድቃል፤

ሸ) ለማህበሩና ለቦርዱ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች ያስፈፅማል፤

ቀ) የማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል፡፡

2) የማህበሩ የስምሪት ክፍልኃላፊ/የስምሪት ሰራተኛ ስልጣንና ተግባር

ማህበሩ የሥምሪት እንቅስቃሴ የሚመራ የስምሪት ክፍል የሚኖረው ሲሆን የክፍል ኃላፊ በስራ አስኪያጁ አቅራቢነት በሥራ አመራር ቦርዱ ሲፀድቅእንዲመደብይደረጋል፡፡ ተጠሪነቱ ለሥራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

ሀ/ የአባል ተሽከርካሪዎችን ሳምንዊ/ ወርሃዊ የሥምሪት ኘሮግራም በኩልነት ላይ በተመሰረተሁኔታ ያዘጋጃል፣ ለአደራጁ አካል አቅርቦ ያፀድቃል፤

ለ/ በወጣውየሥምሪት ኘሮግራም መሠረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፤

ሐ) የተሻለ አገልግሎት ለተጠቃሚው ለማቅረብ የሚያስችል የሥምሪት ጥናት አድርጎ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ/ የማህበሩን አባል ተሽከርካሪዎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል፤

ሠ/ በአባላት ተሽከርካሪዎች ላይ የቴክኒክ ደሕንነትና ብቃትን ቁጥጥር ያደርጋል፣ ተስተካክለውም ለሥምሪት መቅረባቸውን ያረጋግጣል፤

ረ/ በአባላት መካከል በስምሪት አድልዎ ያለመደረጉን ያረጋግጣል፤

ሰ/ ወቅታዊ የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

3) የመረጃና ትራፊክ ደህንነት አገልግሎት ስልጣንና ተግባር

የማህበሩንመረጃዎችን የሚያሰባስብ፣ የሚያደራጅና የሚያቀነባብር የመረጃና ትራፊክ ደህንነት አገልግሎት ክፍል የሚኖረው ሲሆን የሥራ ሃላፊው በሥራ አስኪያጁ አቅራቢነት በሥራ አመራር ቦርዱ ፀድቆ እንዲመደብ ይደረጋል፣ ተጠሪነቱ ለሥራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፣

ሀ/ አጠቃላይ የማህበሩን ተሽከርካሪዎችና የስምሪት እንቅስቃሴ መረጃ ይይዛል፤

ለ/ በአደራጁ አካል በተዘጋጁ ፎርሞች መሠረት መረጃዎችን በጽሕፈት ቤቱ በኩል ያስተላልፋል፤

ሐ/ በአገልግሎት አሰጣጥ የሚከሰቱ የተሽከርካሪ ግጭቶችንና አደጋዎችን ይመዘግባል፤

መ/ ስለትራፊክ ደሕንነት ለአባላቱ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ ያደርጋል፣ በአባላቱ ተሽከርካሪዎች የሚደርሱ አደጋዎችን ለመቀነስ የመንገድ ደህንነትን ለማስፈን አስፈላጊ ስርዓት ነድፎ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሠ/ የሥራ ሪፖርት ያዘጋጃል፣ ለሚመለከተው አካልም ያቀርባል፤

ረ/ በአደራጁ በኩል ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ስድስት

## በየደረጃዉ ያሉ የተቋሙ አደረጃጀቶች ተግባርና ሃላፊነቶች

### 19. የቢሮዉ ተግባርና ሃላፊነቶች

1/ የከተማ ትራንስፖርት ማህበራቱ በወሰዱት ፈቃድ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን መከታተል መቆጣጠር፡፡መመሪያዉንአክብረዉ በማይሰሩ ማህበራት እናየማህበራቱ አባላት ላይ እርምጃ መዉሰድ እንዲሁም በማህበሩ የቅጥር ሰራተኞች እና የቦርድ አመራሮች ላይ እንደአስፈላጊነቱ የዲሲፒሊን እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ማድረግ፤

2/ የማህበሩ አባላት አደረጃጀታቸውና አሰራራቸው ወደ ዘመናዊየንግድ ኩባንያ እንዲሸጋገሩ የአቅም ግንባታ እና የድጋፍ አገልግሎት መስጠት፤

3/ እንደአስፈላጊነቱ የወጣዉን መመሪያ ማሻሻያ ማድረግ፡፡

### 20. የዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያዎች ተግባርና ሃላፊነቶች

1/ የአነስተኛ እና የመካከለኛ ከተሞች ማህበር ለመመስረት ጥያቄ የሚያቀርቡ የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች ያዘጋጁቱን የመመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ መርምሮ በማጽደቅ ፈቃድ መስጠት እና እድሳት ማድረግ፤

2/ ማህበሩበማካሂደዉ አመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በመገኘት በመመሪያዉ መሰረት የስራ አመራር ቦርድ ምርጫ እንዲካሄድ ማድረግና ሌሎች መንግስት የሚያስተላልፋቸዉን መመሪያዎች ማስተላለፍ፤

3/ የከተማ ትራንስፖርት ማህበራቱ በወሰዱት ፈቃድ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን መከታተል መቆጣጠር፡፡መመሪያዉን አክብረዉ በማይሰሩ ማህበራት እና



The ANRS Bureau of Justice

የማህበራቱ አባላት ላይ እርምጃ መዉሰድ እንዲሁም በማህበሩ የቅጥር ሰራተኞች እና የቦርድ አመራሮች ላይ እንደአስፈላጊነቱ የዲሲፒሊን እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ማድረግ፤

4/ የማህበሩ አባላት አደረጃጀታቸውና አሰራራቸው ወደ ዘመናዊ የንግድ ኩባንያ እንዲሸጋገሩ የአቅም ግንባታ እና የድጋፍ አገልግሎት መስጠት፤

5/ በዞኑ ያሉ የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት የፈቃድስረዛ ዉሳኔ መስጠት፤

6/ የወጣዉ መመሪያ ማሻሻያ እንዲደረግበት ለቢሮዉ ግብአት መላክ፡፡

## 21. የሜትሮፖሊታንት ከተሞች ትራንስፖርት ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነቶች

1/ ማህበር ለመመስረት ጥያቄ ለሚያቀርቡ የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች ያዘጋጁቱን የመመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ መርምሮ በማጽደቅ ፈቃድ መስጠት እድሳት ማድረግ፤

2/ ማህበሩ በማካሂደዉ አመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በመገኘት በመመሪያዉ መሰረት የስራ አመራር ቦርድ ምርጫ እንዲካሄድ ማድረግና ሌሎች መንግስት የሚያስተላልፋቸዉን መመሪያዎች ማስተላለፍ፤

3/ የከተማ ትራንስፖርት ማህበራቱ በወሰዱት ፈቃድ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን መከታተል መቆጣጠር፡፡መመሪያዉን አክብረዉ በማይሰሩ ማህበራት እና የማህበራቱ አባላት ላይ እርምጃ መዉሰድ እንዲሁም በማህበሩ የቅጥር ሰራተኞች እና የቦርድ አመራሮች ላይ እንደአስፈላጊነቱ የዲሲፒሊን እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ማድረግ፤

4/ የማህበሩ አባላት አደረጃጀታቸውና አሰራራቸው ወደ ዘመናዊየንግድ ኩባንያ እንዲሸጋገሩ የአቅም ግንባታ እና የድጋፍ አገልግሎት መስጠት፤

5/ በከተማዉ ያሉ የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት የፈቃድ ስረዛ ዉሳኔ መስጠት፤

6/ ማህበራት የሚያቀርቡትን የስራ መርሃ ግብርመርምሮ ማጽደቅና ስምሪቱን በበላይነት ማስፈጸም፤ማሻሻያ የሚያስፈልገዉ መሆኑ ከተመነበት ማሻሻያ ማድረግ፤

7/ የወጣዉ መመሪያ ማሻሻያ እንዲደረግበት ለቢሮዉ ግብአት መላክ፡፡

## 22. የወረዳ መንገድና ትራንስፖርት ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነቶች

1/ አዲስ ማህበር ለመመስረት ወይም አመታዊ እድሳት ጥያቄ ለሚያቀርቡ የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች መረጃ በማደራጀት ለዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያዎች በመላክ ፈቃድ እንዲሰጣቸዉና እድሳት እንዲደረግላቸዉ ማድረግ፤



The ANRS Bureau of Justice

2/ ማህበሩብ ማካሄደዉ አመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በመገኘት በመመሪያዉ መሰረት የስራ አመራር ቦርድ ምርጫእንዲካሄድ ማድረግና ሌሎች መንግስት የሚያስተላልፋቸዉን መመሪያዎች ማስተላለፍ፤

3/ የከተማ ትራንስፖርት ማህበራቱ በወሰዱት ፈቃድ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን መከታተል መቆጣጠር፤ መመሪያዉን አክብረዉ በማይሰሩ ማህበራት እና የማህበራቱ አባላት ላይ እርምጃ መዉሰድ እንዲሁም በማህበሩ የቅጥር ሰራተኞች እና የቦርድ አመራሮች ላይ እንደአስፈላጊነቱ የዲሲፒሊን እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ማድረግ፤

4/ የማህበሩ አባላት አደረጃጀታቸውና አሰራራቸው ወደ ዘመናዊየንግድ ኩባንያ እንዲሸጋገሩ የአቅም ግንባታ እና የድጋፍ አገልግሎትመስጠት፤

5/ ማህበራት የሚያቀርቡትን የስራ መርሃ ግብር መርምሮ ማጽደቅና ስምሪቱን በበላይነት ማስፈጸም፤ ማሻሻያ የሚያስፈልገዉ መሆኑ ከተመነበት ማሻሻያ ማድረግ፤

6/ የወጣዉ መመሪያ ማሻሻያ እንዲደረግበት ለዞን/ለቢሮዉ ግብአት መላክ፡፡

## 23. የዞንከተሞች የትራንስፖርት ልማት ቡድኖች ተግባርና ኃላፊነቶች

1/ ማህበር ለመመስረት ጥያቄ ለሚያቀርቡ የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች ያዘጋጁቱን የመመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ መርምሮ በማጽደቅ ፈቃድ መስጠት እድሳት ማድረግ፤

2/ ማህበሩ በማካሄደዉ አመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በመገኘት በመመሪያዉ መሰረት የስራ አመራር ቦርድ ምርጫ እንዲካሄድ ማድረግና ሌሎች መንግስት የሚያስተላልፋቸዉን መመሪያዎች ማስተላለፍ፤

3/ የከተማ ትራንስፖርት ማህበራቱ በወሰዱት ፈቃድ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን መከታተል መቆጣጠር፡፡መመሪያዉን አክብረዉ በማይሰሩ ማህበራት እና የማህበራቱ አባላት ላይ እርምጃ መዉሰድ እንዲሁም በማህበሩ የቅጥር ሰራተኞች እና የቦርድ አመራሮች ላይ እንደአስፈላጊነቱ የዲሲፒሊን እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ማድረግ፤

4/ የማህበሩ አባላት አደረጃጀታቸውና አሰራራቸው ወደ ዘመናዊ የንግድ ኩባንያ እንዲሸጋገሩ የአቅም ግንባታ እና የድጋፍ አገልግሎት መስጠት፤

5/ ማህበራት የሚያቀርቡትን የስራ መርሃ ግብርመርምሮ ማጽደቅና ስምሪቱን በበላይነት ማስፈጸም፤፡፡ ማሻሻያ የሚያስፈልገዉ መሆኑ ከተመነበት ማሻሻያ ማድረግ፤

6/ የወጣዉ መመሪያ ማሻሻያ እንዲደረግበት ለዞን/ለቢሮዉ ግብአት መላክ፡፡

## 24. የመካከለኛ ከተሞች የትራንስፖርት ልማት ቡድኖች ተግባርና ኃላፊነቶች

1/ አዲስ ማህበር ለመመስረት ወይም አመታዊ እድሳት ጥያቄ ለሚያቀርቡ የከተማ ታክሲ ባለንብረቶች መረጃ በማደራጀት ለዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያዎች በመላክ ፈቃድ እንዲሰጣቸዉና እድሳት እንዲደረግላቸዉ ክትትል ማድረግ፤

2/ ማህበሩ በማካሄደዉ አመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በመገኘት በመመሪያዉ መሰረት የስራ አመራር ቦርድ ምርጫ እንዲካሄድ ማድረግና ሌሎች መንግስት የሚያስተላልፉቸዉን መመሪያዎች ማስተላለፍ፤

3/ የከተማ ትራንስፖርት ማህበራቱ በወሰዱት ፈቃድ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን መከታተል መቆጣጠር፤ መመሪያዉን አክብረዉ በማይሰሩ ማህበራት እና የማህበራቱ አባላት ላይ እርምጃ መዉሰድ እንዲሁም በማህበሩ የቅጥር ሰራተኞች እና የቦርድ አመራሮች ላይ እንደአስፈላጊነቱ የዲሲፒሊን እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ማድረግ፤

4/ የማህበሩ አባላት አደረጃጀታቸውና አሰራራቸው ወደ ዘመናዊ የንግድ ኩባንያ እንዲሸጋገሩ የአቅም ግንባታ እና የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል፤

5/ ማህበራት የሚያቀርቡትን የስራ መርሃ ግብር መርምሮ ማጽደቅና ስምሪቱን በበላይነት ማስፈጸም፤ ማሻሻያ የሚያስፈልገዉ መሆኑ ከተመነበት ማሻሻያ ማድረግ፤

6/ የወጣዉ መመሪያ ማሻሻያ እንዲደረግበት ለዞን/ለቢሮዉ ግብአት መላክ፡፡

# ክፍል ሰባት

# ዲስፒሊን

## 25. የዲስፒሊን እርምጃ የሚያስወስዱ ተግባራቶች

1/ የማህበራት ሰራተኞችበተመለከተ

ሀ) የማህበሩ ሰራተኞች ሰራተኝነታቸውን ሊያረጋግጥ የሚችል በፎቶ ግራፍ ተደገፈ መታወቂያ አለማዘጋጀት፤

ለ) ለማህበሩ ተሽከርካሪዎች የማህበሩ አርማ አለማሳተም፤

ሐ) ቢሮዉ እንዲላክለት የሚጠይቃቸዉን መረጃዎችና ሪፖርቶች በወቅቱ አለመላክ፤

መ) የማህበር አባል ለመሆን መመዘኛውን የሚያሟሉ የከተማ ታክሲ ባለንብረቶችን በአባልነት ተቀብሎ አለማስተናገድ፤

ሠ) አባሉ መልቀቂያ እንዲሰጠዉ ሲጠይቅ በተቀመጠዉ ጊዜ ዉስጥ መልቀቂያ አለመስጠት፤

ረ) ከሌላ ማህበር ለቆ መምጣቱን በቂ መረጃ እያለዉ ክሊራንስ ሳይጠየቅ በአባልነት መመዝገብ፤

ሰ) መመሪያው /መተዳደሪያ ደንቡ/ ከሚፈቀደው በላይ የማህበር አመራር አካላት የቆይታ ጊዜ ማራዘም፤

ሸ) ከስራ አመራር ቦርድ ዉሳኔ ዉጪ የማህበሩን ገንዘብ ስራ ላይ መዋል፤

ቀ) በማህበሩ ዉስጥ በአባልነት የተመዘገበ የተሽከርካሪ ባለንብረትን ቅጥር ሰራተኛ ማድረግ፤

በ) ፈቃድ ከተሰጠዉ/ ከታደሰለት/ በኋላ የሰዉ ሃልና የቢሮ አደረጃጀት አንድሎ መገኘት፤

ተ) የማህበሩ እዉቅና በተሰጠዉ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ በማህበሩ ስም የባንክ አካውንት አለመክፈት፤

ቸ) በማህበሩ ስም በተከፈተዉ አካዉንት ገንዘብ ገቢ አለማድረግ፤

ነ) በታክሲ ማሽከርከር ተግባር ላይ የተሰማሩ አሽከርካሪዎች የሚያደርሡትን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ የግንዛቤ ማዳበሪያና የተሃድሶ ስልጠና የሚያገኙበትን መንገድ አለማመቻቸት፤

ኘ) በዚህ መመሪያ ከተቀመጠዉ የአባልነት ክፍያ በላይ ገንዘብ መጠየቅ/ መቀበል፤

አ) የማህበሩ ቅጥር ሠራተኞች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነትና ተግባር እንዲወጡ በማድረግ በሚፈፅሟቸው የስነ ምግባር ችግሮች በመከታተል የእርምት እርምጃ አለመዉሰድ፡፡

2/ የማህበሩ አባል በተመለከተ

ሀ) የስራ አመራር ቦርድ የሚወስነዉን ልዩ ልዩ ክፍያ አለመክፈል፤

ለ) በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የስልጣን ዉክልና በተሰጠዉ የስራ አመራር ቦርድ የሚተላለፉ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን አለመፈጸም፤



The ANRS Bureau of Justice

ሐ) በመንግስት የሚወጡ ህጎች ደንብና መመሪያዎችን አክብሮ በስራ ላይ ማዋል፡፡

3/ በማህበራት ሰራተኞች እና አባላቶች ላይ የሚወሰድ የዲስፕሊን ቅጣቶች የከተማ ታክሲ ተሽከርካሪ ባለንብቶች ማህበር ቅጥር ሰራተኞች እና አባላት በዚህ መመሪያ የተገለጹትንጥፋቶች በሚፈጽሙበት ወቅት የዲሲፒሊን እርምጃ ይወስድባቸዋል፤ የሚወሰድባቸዉ የዲሲፒሊን እርምጃከዚህ ቀጥሎ በሰፈረዉ ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነቶች | የሚወሰድ የዲስፕሊን እርምጃ አይነት | | | | እርምጃ የሚወሰድበት አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ለመጀመሪያ ጊዜ | ለ2ኛ ጊዜ | ለ3ኛ ጊዜ | ለ4ኛ ጊዜ | |
| 1 | ለማህበሩ ሰራተኞች ሰራተኝነታቸውን የሚያረጋግጥ በፎቶ ግራፍ የተደገፈ መታወቂያ አለማዘጋጀት | 500 | 800 | 1500 | የሰራተኛዉ ቅጥር ይሰረዛል | ስራ አስኪያጅ/ የኦፕሬሽን ክፍል ሃላፊ/ የስምሪት ሰራተኛ |
| 2 | በማህበሩ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚለጠፍ የማህበሩን አርማ አለማሳተም | 500 | 800 | 1500 | የሰራተኛዉ ቅጥር ይሰረዛል | ስራ አስኪያጅ/ የኦፕሬሽን ክፍል ሃላፊ/ የስምሪት ሰራተኛ |
| 3 | ቢሮዉ እንዲላክለት የሚጠይቃቸዉን መረጃዎችና ሪፖርቶች በወቅቱ አለመስጠት | 500 | 1000 | 1500 | የሰራተኛዉ ቅጥር ይሰረዛል | ስራ አስኪያጅ/ የኦፕሬሽን ክፍል ሃላፊ/ የስምሪት ሰራተኛ |
| 4 | አባላት መልቀቂያ እንዲሰጣቸዉ ሲጠይቁ መልቀቂያ አለመስጠት፤ | 500 | 1000 | 1500 | የሰራተኛዉ ቅጥር ይሰረዛል | ስራ አስኪያጅ/ የኦፕሬሽን ክፍል ሃላፊ/ የስምሪት ሰራተኛ |
| 5 | መመሪያ በሚፈቀደው መሰረት የአባልነት ጥያቄ አለመቀበል | 1000 | 1500 | 2000 | የሰራተኛዉ ቅጥር ይሰረዛል | ስራ አስኪያጅ/ የኦፕሬሽን ክፍል ሃላፊ/ የስምሪ |



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የሕግ ማርቀቅና ማጠቃለያ ዳይሬክቶሬት

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ሰራተኛ |
| 6 | ከሊላ ማህበር ለቆ መምጣቱን በቂ መረጃ እያለዉ ክሊራንስ ሳይጠየቅ በአባልነት መመዝገብ | 1000 | 1500 | 2000 | የሰራተኛዉ ቅጥር ይሰረዛል | ስራ አስኪያጅ የኦፕሬሽን ክፍ ሃላፊ/ የስምሪ ሰራተኛ |
| 7 | መመሪያው /መተዳደሪያ ደንቡ/ ከሚፈቀደው በላይ የማህበር አመራር አካላት የቆይታ ጊዜ ማራዘም | 1000 | የማህበሩ ፈቃድ ይሰረዛል | | | ስራ አመራ ቦርድ |
| 8 | ከስራ አመራር ቦርድ ዉሳኔ ዉጪ የማህበሩን ገንዘብ ማባከን | 1000 | ቅጥሩ ተሰርዞ በህግ ይጠየቃል | | | ስራ አስኪያጅ የኦፕሬሽን ክፍ ሃላፊ/ የስምሪ ሰራተኛ |
| 9 | ፈቃድ ከተሰጠዉ/ ከታደሰለት/ በኋላ የሰዉ ሃልና የቢሮ አደረጃጀት አጓድሎ መገኘት | 500 | 1000 | የሰራተኛ ዉ ቅጥር ይሰረዛል | | ስራ አስኪያጅ የኦፕሬሽን ክፍ ሃላፊ/ የስምሪ ሰራተኛ |
| 10 | በማህበሩ ዉስጥ በአባልነት የተመዘገበ የተሽከርካሪ ባለንብረት በቅጥር ሰራተኛነት መመደብ | 500 | 1000 | የሰራተኛ ዉ ቅጥር ይሰረዛል | | ስራ አስኪያጅ የኦፕሬሽን ክፍ ሃላፊ/ የስምሪ ሰራተኛ |
| 11 | የማህበሩ እዉቅና በተሰጠዉ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ በማህበሩ ስም የባንክ አካውንት አለመክፈት | 500 | 1000 | የሰራተኛ ዉ ቅጥር ይሰረዛል | | ስራ አስኪያጅ የኦፕሬሽን ክፍ ሃላፊ/ የስምሪ ሰራተኛ |
| 12 | በማህበሩ ስም በተከፈተዉ አካዉንት ገንዘብ ገቢ አለማድረግ | 1000 | | ቅጥሩ ተሰርዞ በህግ | | ስራ አስኪያጅ የኦፕሬሽን ክፍ ሃላፊ/ የስምሪ |

| | | | | ይጠየቃል | | ሰራተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 13 | በታክሲ ማሽከርከር ተግባር ላይ የተሰማሩ አሽከርካሪዎች የሚያደርሱትን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ የግንዛቤ ማዳበሪያና የተሃድሶ ስልጠና የሚያገኙበትን መንገድ አለማመቻቸት | 500 | 1000 | 2000 | የሰራተኛዉን ቅጥር ይሰረዛል | ስራ አስኪያጅ/ የኦፕሬሽን ክፍል ሃላፊ/ የስምሪት ሰራተኛ |
| 14 | በዚህ መመሪያ ከተቀመጠዉ የአባልነት ክፍያ በላይ ገንዘብ መጠየቅ/ መቀበል | 500 | 1000 | 1500 | የሰራተኛዉን ቅጥር ይሰረዛል | ስራ አስኪያጅ/ የኦፕሬሽን ክፍል ሃላፊ/ የስምሪት ሰራተኛ |
| 15 | የማህበሩ ቅጥር ሠራተኞች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነትና ተግባር እንዲወጡ በማድረግ በሚፈፅሟቸው የስነ ምግባር ችግሮች በመከታተል የእርምት እርምጃ አለመዉሰድ | 500 | 1000 | 1500 | የሰራተኛዉን ቅጥር ይሰረዛል | ስራ አስኪያጅ/ የኦፕሬሽን ክፍል ሃላፊ/ የስምሪት ሰራተኛ |
| 16 | በጠቅላላ ጉባኤዉ የተወሰኑ ልዩ ልዩ ክፍያዎችን አለመክፈል | 200 | 300 | 400 | ከማህበር አባልነትመሰረዝ | የማህበር አባል |
| 17 | በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የስልጣን ዉክልና በተሰጠዉ የስራ አመራር ቦርድ የሚተላለፉ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን አለመፈጸም | 200 | 300 | 400 | ከማህበር አባልነት መሰረዝ | የማህበር አባል |
| 18 | በመንግስት የሚወጡ ህጎች ደንብና መመሪያዎችን አክብሮ በስራ ላይ ማዋል | 200 | 300 | 400 | ከማህበር አባልነት መሰረዝ | የማህበር አባል |
| 19 | ሌሎች የወጡ ህጎችን አክብሮ አለመስራት | 500 | 1000 | 1500 | የሰራተኛዉን ቅጥር ይሰረዛል | ስራ አስኪያጅ/ የኦፕሬሽን ክፍል ሃላፊ/ የስምሪት ሰራተኛ |

# ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 26. ልዩ ሁኔታ

1/ የአንድ የማህበር አባል በሞት ቢለይ አባሉ ወራሽ ካለ እና ህጋዊ የዉርስ ማስረጃ ከሚመለከተዉ ተቋም ማምጣት ከቻለ ወራሹ የምዝገባ ክፍያ ሳይከፍል የማህበሩ አባል ሆኖ እንዲቀጥል ይደረጋል፤

2/ የከተማ ታክሲ ትራንስፖርት ማህበራት ፈቃድ የሚሰጡ እና እድሳት የሚያደርጉ የዞን መንገድና ትራንስፖርት መመሪያዎች፣ 3ቱ ሜትሮፖሊታንት ከተሞች ትራንስፖርት ጽ/ቤት እና የዞን ከተማ ትራንስፖርት ልማት ቡድኖች ናቸዉ፤የወረዳ መንገድና ትራንስፖርት ጽ/ቤቶች እናየመካከለኛ ከተሞች ትራንስፖርት ልማት ቡድኖች በማህበር የመደራጀት ጥያቄ በመቀበል መረጃዉን ለዞንመንገድና ትራንስፖርት መምሪያ ልከዉ ዞኑ ፈቃድ ይሰጣል/ እድሳት ያደርጋል፤

3/ ተቀጣሪ ሰራተኞች በተቀጠሩበት ማህበርተሽከርካሪ ሊኖራቸዉ አይገባም ፤

4/ ከአንድ በላይ ባጃጅ/ ታክሲ ያለዉ ባለሃብት ሁሉንም ተሽከርካሪዎች በአንድባጃጅ/ ታክሲ ማህበር ዉስጥ ማስመዘገብ አለበት፤

5/ ከአንድ በላይ ባጃጅ/ ታክሲ ያለዉ ባለሃብት በአንድ ባጃጅ/ ታክሲ ማህበር ዉስጥ መመዝገብ የማያስችል ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜየባጃጅ/ የታክሲ ባለንበረት በቦርድ አመራርነት የሚመረጠዉ በአንድ ባጃጅ/ ታክሲ ማህበር ብቻ ነዉ፤

6/ ከከተማ ታክሲ ባልንብረቶች ዉክልና የወሰዱ ሰዎች በማህበሩ የስራ አመራር ቦርድ የመመረጥ ሆነ የመምረጥ መብትየላቸዉም፤

7/ ቢሮዉየኮድ- 3 ተሽከርካሪ ባለንብረቶች የከተማ ታክሲ አገልግሎት እንዲሰጡ ፈቃድ ከሰጠ ባለንብረቶቹ ለብቻቸዉ ወይም ከኮድ -1 ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ጋር በመሆን ማህበር ሊመሰርቱ ይችላሉ፤

8/ የከተማ ታክሲ ትራንስፖርት ማህበራት ተጨማሪ አባል መመዝገብ የሚችሉት ፈቃድ ከሰጣቸዉ መምሪያ ወይም ጽ/ቤት እዉቅና ሲያገኙ ነዉ፤

9/ ስምሪቱን በአግባቡ ለመምራት እንዲያስችል በአንድ ከተማ ዉስጥ ማህበር ለማቋቋም/ለመመስረት/ የሚያስችል የባጃጅ እና የታክሲ ቁጥር ካለጠፋ በስተቀር

ማንኛዉም የከተማ ታክሲ ተሽከርካሪ ባለንብረት በማህበር መደራጀት አለበት፤ በማህበር ካልተደራጀ ስምሪት ሊሰጠዉ አይገባም፤ ሆኖም ግን በአንድ ከተማ ዉስጥ ማህበር ለመመስረት የማያስችል ሁኔታ በሚፈጠርበት ወቅት እያንዳንዱ የከተማ ታክሲ ተሽከርካሪ ባለንብረት በየደረጃዉ ላለዉ የመንገድና ትራንስፖርት ጽ/ቤት ስምሪት በማስፈቀድ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

## 27. የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድና አፈጻጸም

1/ በዚህ መመሪያ የተገለጹትን ጥፋቶች የማህበሩ ሰራተኞች በሚፈጽሙበት ወቅት የተወሰነባቸዉን ገንዘብ ከራሳቸዉ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ እንዲያደርጉ ቢሮዉ ለማህበሩ ይገልጻል፡፡በደብዳቤዉ መሰረት ጥፋት የፈጸመዉ ሰራተኛ ቅጣቱን ለመንግስት ገቢ ማድረጉን የስራ አመራር ቦርድ ሃላፊነት ይወስዳል፤

2/ ከላይበዚህ ንዑስ አንቀጽ 1የተገለጸዉ ቢኖርም ይህንን ቅጣት ለመፈጸም ፈቃደኛ ያልሆኑ የቅጥር ሰራተኞችና ሌላ ለመባረር የሚያበቃ ጥፋት መፈጸማቸዉ ሲረጋገጥ

ሀ) የስራ አስኪያጅ በስራ አመራር ቦርድ

ለ) የሌሎች ሰራተኞችን በስራ አስኪያጅ የማባረር ዉሳኔ ይሰጣል

ሐ) ከማህበር አባልነት መሰረዝ በማህበሩ ስራአስኪያጅ ዉሳኔ ይሰጣል

3/ በዚህ መመሪያ የተገለጹትንጥፋቶች የማህበሩ አባላት በሚፈጽሙበት ወቅት ማህበሩ በዉስጥ መተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የሚሳልፈዉ ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮዉ መቅጣት እንዲችል ማህበሩ ጥፋት የፈጸሙትን አባላትን ዝርዝር ማሳወቅ አለበት፤

4/ በዚህ መመሪያ የተገለጹትንየስነምግባር ወይም የስነ-ስርአት ጉድለቶች ባለማክበሩ ምክንያት የገንዘብ ቅጣት የተጣለበት የማህበር አባል ወይም ሰራተኛ በአንድ ሳምንት ዉስጥ ቅጣቱን መክፍል አለበት፤

5/ ከላይ በአንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 3 በተገለጸዉ አግባብ ክፍያ የማይፈጽም የማህበር አባል ወይም ሰራተኛ ለተጨማሪ ቅጣት ይዳረጋል፡፡ ይህዉም ለእያንዳንዱ ለአሳለፈበት 15 ቀናት ብር 50 እየታሰበ እንዲቀጣ ይደረጋል፤

6/ የቅጣቱ ሪከርድ የሚቆይበት ጊዜ በተመለከተ

ሀ) የመጀመሪያ ጊዜ ቅጣት የቆይታ ጊዜ ቅጣቱ ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ለ12 ወራት ይሆናል፤

ለ) የሁለተኛ ጊዜ ቅጣት የቆይታ ጊዜ ቅጣቱ ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ለ18 ወራት ይሆናል፤

ሐ) የሶስተኛ ጊዜ ቅጣት የቆይታ ጊዜ ቅጣቱ ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ለ24 ወራት ይሆናል፤

መ) የመባረር ወሳኔ የተሰጠዉ ሰራተኛ ወይም የማህበር አባል ተመልሶ መቀጠር ወይም አባል መሆን የሚችለዉ ከ 24 ወር በኋላ ይሆናል፡፡

## 28. የመተባበር ግዴታና የወንጀል ሀላፊነት

1/ ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ ለማስፈጸም ስልጣን ከተሰጣቸው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፤

2/ ይህን መመሪያ የጣሰ ወይም ያሰናከለ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር በተደነገገው ሠንጠረዥ መሰረት ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በከተማ ትራንስፖርት ላይ በሚፈጽማቸው ሌሎች ወንጀሎች አግባብ ባለው ህግ ከመጠየቅ አይድንም፡፡

## 29.የሽግግር ጊዜ

የከተማ ትራንስፖርት ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር የአገልግሎት አሰጣጥ እና የአሰራርመመሪያ ቁጥር 7/2005 ዓ.ም መሰረትፈቃድ የተሠጣቸዉ የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት ይህ መመሪያ ጸድቆ ስራ ላይ ከዋለበትበ6ር ጊዜ ዉስጥ በዚህ መመሪያ መሰረት የቢሮና የሰዉ ሃይል አደረጃጀት ማስተካከልአለባቸዉ፡፡በዚህ ጊዜ ዉስጥ አደረጃጀቱን ያላስተካከለማህበር የማህበሩ ፈቃድ አይታደስም፡፡

## 30. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

1/ ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም ሌላ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥበተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፤

2/ የከተማ ትራንስፖርት ተሽከርካሪ ባለንብረቶች ማህበር የአገልግሎትአሰጣጥ እና የአሰራር መመሪያ ቁጥር 7/2005 ዓ.ም በዚህ መመሪያ ተሽራል፡፡

## 31. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 32. መመሪያው ስራ ላይ ስለሚውልበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ካጸደቀበት ከነሃሴ 1/ 2012 ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ በፍትሕ ቢሮ ከተመዘገበበትና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኃላ ተፈጻሚነት የሚኖረው በአማራ ክልል መንገድ፣ ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ቢሮ ድረ ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

**ደሳለኝ ወዳጅ**

**የአብክመ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ**